አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አ.ማ.

LION INTERNATIONAL BANK S.C.

# የአንበሳ ኢንተርናሽናል አክሲዮን ማህበር

# የባለአክሲዮኖች 21ኛ መደበኛ እና 7ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች የስብሰባ ጥሪ

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አንቀጽ 366(1)፣ 367(1)፣ አንቀጽ 370 እና አንቀፅ 394 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመስረቻ ጽሑፍ አንቀፅ 11(7) መሰረት የአንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ አክሲዮን ማህበር የባለአክስዮኖች 21ኛ ዓመታዊ መደበኛ እና 7ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤዎች ጥቅምት 22 ቀን 2018 ዓ.ም ከጠዋቱ 2:00 ሠዓት ጀምሮ በሸራተን አዲስ ሆቴል ላሊበላ የስብሰባ አዳራሽ ይካሄዳሉ፡፡ በመሆኑም ባለአክሲዮኖች በተጠቀሰው ቀን፣ ቦታ እና ሰዓት ተገኝተው በጉባዔው እንዲሳተፉ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን በአክብሮት ያቀርባል፡፡

## 1. <u>ባንኩን የሚመለከቱ መረጃዎች</u>

1.1. የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥርያ ቤት አድራሻ: አዲስ አበባ፣ የካ ክ/ከተማ፣ ወረዳ 07፣ የቤት ቁጥር አዲስ፣ የድረ-ገፅ አድራሻ: https://anbesabank.com

1.2. የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር: MT/AA/3/0055690/2015

1.3. የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡ ብር 5,001,804,048.00

1.4. የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፡ ብር 5,001,804,048.00

## 2. <u>የ21ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች</u>

2.1. የጉባኤውን አጀንዳዎች ማፅደቅ፣

2.2. የዳይሬክተሮች ቦርድ የጥቆማ እና አስመራጭ ኮሚቴ መምረጥ፣

2.3. በባንኩ ውስጥ የተደረጉ የአክሲዮን ዝውውሮችንና የአዳዲስ አክሲዮኖችን ሽያጭ ማፅደቅ እና አዳዲስ ባለአክስዮኖችን መቀበል፣

2.4. እ.ኤ.አ የ2024/2025 የሒሳብ ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

2.5. እ.ኤ.አ የ2024/2025 የሒሳብ ዓመት የውጪ ኦዲተሮች ሪፖርት ማድመጥና ተወያይቶ ማጽደቅ፣

2.6. እ.ኤ.አ በ2024/2025 የሒሳብ ዓመት የተጣራ ትርፍ አደላደልና አከፋፈል ላይ ውሳኔ መስጠት፣

2.7. እ.ኤ.አ የ2024/25 በጀት ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ዓመታዊ ክፍያ ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

2.8. እ.ኤ.አ የ2025/26 በጀት ዓመት የዳይሬክተሮች ቦርድ ወርሐዊ አበል ላይ ተወያይቶ መወሰን፣

2.9. ባንኩን ለሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት የሚያገለግሉ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላትን መምረጥ፣ እና

2.10. የጉባኤውን ቃለ ጉባኤ ማፅደቅ ና ቸው፡፡

## 3. <u>የ7ኛ አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ አጀንዳዎች</u>

3.1. የጉባኤውን አጀንዳ ማፅደቅ፣ እንዲሁም

3.2. በወረቀት የወጡ አክሲዮኖችን በግዑዝ አልባ አክሲዮኖች ሊተኩ ስለሚችሉበት ሁኔታ መወሰን ናቸው፡፡

## 4. <u>ማሳሰቢያ</u>

4.1. በ20ኛው የባለአክሲዮኖች ጠቅላላ ጉባኤ የፀደቀው የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምልመላና ምርጫ ማስፈፀሚያ የአሰራር ደንብ ከባንኩ ድረ-ገፅ www.anbesabank.com ላይ ማግኘት ይችላሉ፡፡

4.2. በጉባኤው በግንባር መገኘት የማትችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻችሁን ስልጣን ባለው የመንግስት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ ውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶኮፒ በመያዝ ወይም በንግድ ሕግ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባኤው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት 22 ማዞሪያ ሊከስ ፒላዛ ህንፃ ውስጥ በሚገኘው የባንኩ ዋና መስሪያ ቤት የሕግ አገልግሎት መምሪያ በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅፅ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባኤው ተካፋይ መሆንና ድምጽ መስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡ ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባኤ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

4.3. የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባኤው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ ወይም ፋይዳ መታወቂያ ዋናውንና ቅጂ በመያዝ በጉባኤው ላይ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያውያን መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቀን ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳውቃለን፡፡

4.4. የሚወከሉ ባለአክሲዮኖች የሚቀበሉት የውክልና መጠን የራሳቸውን አክሲዮን ጨምሮ ከባንኩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ ከአስር (10) በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

4.5. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀፅ 20/3 መሰረት የባንኩ የቦርድ አባላትና ሰራተኞች በማናቸውም ባለአክሲዮኖች ጉባኤ ላይ ማንኛውም ባለአክስሲዮን ወክለው መገኘት አይችሉም፡፡

4.6. ለምዝገባ ቅልጥፍና ሲባል ባንኩ የባለአክስዮኖችን የመለያ ቁጥር ባስመዘገባችሁት የተንቀሳቃሽ ስልክ የሚልክ ሲሆን፣ የመለያ ቁጥራችሁን በስብሰባው ዕለት ይዛችሁ እንድትቀርቡ በአፅንኦት እንጠይቃለን፡፡

**<u>የዳይሬክተሮች ቦርድ</u>**

**<u>አንበሳ ኢንተርናሽናል ባንክ</u>**

**<u>የስኬትዎ አጋር!</u>**